**የረቡዕ ር 25 1997 ማርች 2 2005**

## የፍኖተ ሐተታ

## የድርጅቶች ሚና---ትግሉን መምራት ወይስ ጭራ መሆን?

በየትኛውም ሀገር ቢሆን እድ ጭቁን ሕዝብ በተለመደው መንገድ አልገዛም ብሎ ሲወስንና ለውጥን ሲሻና ገዢው ቡድንም ከዚህ በተነሳና በራሱም ቀውስ ምክንያት በዱሮው መንገድ መቀጠል-መግዛት ሲያቅተው ለለውጥ አስፈላጊ የሆነው ተጨባጭ ሁኔታ ተሟልቷል ማለት ይቻላል፡፡ ይህን ሁኔታ ግን ወደ ተጨባጭ ለውጥ ለመተርጎም ህሊናዊ ሁኔታ ተሟልቶ መገኘት አለበት፡፡ ይህም ማለት ሕዝቡ የትግል የለወጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል ማለት ነው፡፡ ድርጅት ያሻዋል፤ መደራጀት ያስፈልገዋል ማለት ነው፡፡ የቀውስ ሁኔታ ወደ ለውጥ እንዲያመራ የሕዝብ ትግል በሕዝብ ድርጅት መመራት አለበት፡፡

ይህ ሁሉ የፖለቲካ ሀ ሁ ነው፡፡ ዛሬ በሀገራችን የፖለቲካ ትርጉሙና ይዘቱ የጠፋቸውና ከአፍንጫቸው አርቀው ማየት ተስኗቸው ከአድማስ ባሻገር ያለውን ሊያማትሩ የሚዳዱ በየመድረኩ አለን አለን እያሉ ነውና ፖለቲካ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ  ደግመን ደጋግመን መግለፁ የግድ እንደሆነው ሁሉ ድርጅት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ማድረጉ አስፈልጓል፡፡ ማንም ሰው ተሰባስቦ ድርጅት የመመስረት መብቱ በወያኔ ቢታደግም በዴሞክራሲ የተጠበቀ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያወቁ መስሏቸው ኢትዮጵያና ሕዝቧ ከዚህ ቁጥር በላይ ድርጅት አያስፈልጋትም ብለው ሊወስኑ የተነሱ እንዳሉ ብንታዘብም በመሰረቱ በአንድ ሀገር ምን ያህል የፖለቲካ ድርጅት ሊኖርና ሊንቀሳቀስ እንደሚችል የሚወስነው ማንም ኃይል ሳይሆን ሕዝብና የሀገሪቷ ተጨባጭ ሁኔታ ነው፡፡ ድርጅቶች የሕዝብ ደጋፍ ካገኙና ፕሮግራማቸው ቦታ ካለው፤አድማጭ ካገኘ ህልውናቸው ይጠበቃል፡፡ በአሜሪካ ሁለት--ያውም ተመሳሳይ-- ድርጅት ወይም ፓርቲ ስላለ ብቻ በሀገራችንም ይህንኑ ቀድተን ቀይ ፊታውራሪ ወይ ደጃዝማች በሚል ጌቶችን ማቀያየር መገደድ የለብንም፡፡ ሀገሪቷ ደህ ናትና የድርጅትም ድህ ትሁን ብሎ ጎወሰን ደግሞ ከዴሞክራሲ ጋር ግንኙነት ያለወ ካለመሆኑ ሌላ እይታችንን ከአሜሪካ ወደ አውሮጳ እንኳን ብንወስድ የድርጅቶች በብዛት መንቀሳቀስን እውነታ መገንዘብ እንችላለን፡፡

ድርጅት በየዓይነቱ ነው፡፡ የገዢዎችን ጥቅም ማለትን የጨቋኞችን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚመሰረቱ ድርጅቶች አሉ፡፡ በሀገራችን ለምሳሌ ህወሓትና ኢሕአዴግ ከነተለጣፊዎቻቸው በዚህ ይፈረጃሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የልዩ ልዩ መደቦችን ጥቅም አስጠባቂ ናቸው፡፡ ለብሄረሰባችን ቆምን ባዮች በርካታ ድርጅቶች ለጭዉኖች ሳይሆን ለዚያ ብሄረሰብ ንዑስ ከበርቴዎችና ምርጦች ጥቅም የቆሙ ናቸው፡፡ የመጨረሻ ግባቸው ቢሳካላቸው ለሕዝብ አይፈይዱም፡፡ ሕዝብ ላይ የሚጫኑ አምባገነኖች ይሆናሉ፡፡ ይህ በየት አንደታየ  እየታየም እንዳለ ምሳሌ ሙ/ቅስ አያሻንም፡፡ አንድ ድርጅት በእርግጥም የሕዝብ ድርጅት ነው፤ሕዝባዊ መስመር አለው ለማለት ካወጣው ፕሮግራም ባሻገር ተጨባጭ የትግል ሚናውን መመርምር ያስፈልጋል፡፡ ከስራው ተነስተን ነው ይዘቱን የምንደመድመው፡፡ ትገሉን እየመነራ ነው ወይስ የትገሉ ጭራ ሆኖ ግንባር የቀደመውን የሕዝብ ትግል ለማዳፈን ወይም ለማቀዝቀዝ ይሰራል የሚለው መመለስ አለበት፡፡ በሀገራችን በአሁነ ቋ ጊዜ

በተቃዋሚ ድርጅቶች የተደረጉ ስብሰባዎችን ስናጤን ሕዝብ ወድሞ መሪ ነን ባይ ድርጅቶች ደግሞ ሲጓተቱና ጭራ ሆነው ትግሉን ሲያደናቅፉ እየታዘብን ነው፡፡ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሉኡ ጊዜ ወያኔን በተመለከተ ምንም ብዥታ የለውም ማለት ይቻላል፡፡ ድጋፍ አለኝ ብሎ ጎለስ ይመፃደቅበት በነበረው በትግራይ እንኳን ለከረሳቸው ካደሩ ካድሬዎቹና ቅጥረኞቹ ውጪ አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ይህንን አገዛዝ ጠልቶታል፡፡ መለስ ዜናዊ በተዓምር ዴሞክራሲያዊ ሆኖ በሀገራችን ነፃ ምርጫ እንዲካሄድም ይስማማል ብሎ የሚያምን ሕዝብ የለም ማለት ስንችል ግን ይህንን ቅዠት ደግሞ ሕልም አድርገው ሊያቅፉ የሚራወጡ ድርጅቶችን እያየን ነው፡፡ በድርድርና በባዕድ ተፅዕኖ መለስ በሰላም ስልጣኑን ይለቃል ብለው የሚያስቡ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን በመራራ ትግል ካልሆነ ወያኔ ከቤተመንግስት አይወጣም ባይ ግን ብዙሀኑ ሕዝብ ነው፡፡ ብዥታ የድርጅቶች፤ንቃት የሕዝብ በሆነበት ተጨባጭ ሁኔታ የትግሉ ሂደት ጎርባጣ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ድርጅቶች ያልተከፈተ የለውጥ በር ገርበብ ብሎ ከታያቸው፤ መረር ላለው ትግል ሀሞቱም ወኔውም ካጠራቸው፤ የመሰዋት አዝማሚያ ጭምት ካደረጋቸው፤ ከርቸሌና ቃሊቲን አታሳየ  አምላኬ ብለው ፀሎት ካበዙ ሕዝብን ሊመሩ ቀርቶ የሕዝብ ትግል ላይ የሚደቀኑ ጋሬጣዎች ናቸው፡፡ የሕዝብ ድርጅት ከሕዝብ ተዋህዶ፤ ሕዝብን አነሳስቶ፤ የሕዝብን መከራ ኖሮ፤ ታግሎና ተሰቃይቶ ትግሉን የሚያፋፍመና አስፈላጊውን መስዋዕትነት የሚከፍል ነው፡፡ ፈረንጆች ሲተርቱ የእሳቱ ሙቀት ከፀናብህ/ሽ ከማድቤቱ ውጥውጪ ይላሉ፡፡ የሕዝብን ትግል መምራት ማለት በየአዳራሹ ከረባት አስሮ ከገዢዎች ጋር መከራከር ወይም በየባዕድ ኤምባሲ ኮክቴል ግብዣ ላይ መደስኮር፤ በየጋዜጣው ገዢውን ቡድን በሂስ መጥረብ ማለት አይደለም፡፡ ድርጅት ማለት ከራስ በላይ አራት አምስቱን ሰብስቦ በወረቀት ነብርነት አገዛዙ  ለማስፈራራት መከጀልም አይደለም፡፡

የቅርብ ታሪካችን የትግል ድርጅቶች ምን እንደሚመስሉ በበቂ አሳይቶናል፡፡ ለሕዝብ ቆመው የታገሉትን አንተውና ለከይሲ ግባቸው ተደራጅተው የነበሩትን እነ ወያኔን እንኳን ብናይ ሳይታገሉ የደረሱበት አልደረሱም፡፡ ዛሬ ስልጣም ሲይዙ ሕዝቡ መሰዋት ሰልችቶታል፤ሰላም ናፍቋል ወዘተ እያሉ ቢለፍፉም ትላንት ጫካ ሳሉ ግን “አደዬ ክላሺኔ” ይሉ እንደነበርና ብረት አልጨብጥ ያለውንም ሰላም ይነሱ እነደነበር የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ ለእነ መለስ እኩይ ዓላማ ጨዳ የሆነው የትግራይ ወጣት ሁለኩ ስለ ሰላም ተሰብኮ አባል የሆነ አልነበረም፡፡ ዛሬ አምርሮ መታገል በሚገባንና ሀገራችንን ታይቶ ከማያውቅ ጥፋት መዳነ. ሲኖርብን ከመሰሪው ገዢ ቡደብ በባሰ ሕዝብ ሰላም ናፍቋልና ያመረረ ትግልን አታንሱብን ባይ ተቃዋሚ ድርጅቶች አሉ፡፡ ይህ ነው የገባንበት ደይን፡፡ ጥያቄው ብረት ማንሳት አለማንሳት ላይ አይደለም፡፡ የመለስ በድን በብረት እንጂ በሌላ አይወገድም ብለው የደመደሙትን ከዚሁ መደምደሚያ ያደረሳቸው ራሱ አረመኔው ቡድንና ድርጊቱ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ዋናው ሀቅ ግን ሕዝብ ለመብቱ መታገል አልሰለቸውም የሚለው ነው፡፡ ከብረቱ ትግል በመለስ ሊደረግ የሚችለውን አርድ አንቀጥቅጥ የሕዝብ አመፅ እውን እናደርጋለን ሲሉ የተደመጡ የአንዳንድ  የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ይህን ሊያደርጉ ቀርቶ የለሆሳስ እምቢታንም ማሰማት ተስኖአቸው የመለስን የምርጫ ቧልት ከአንጋነሰንገሱ ለማጀብ እየተሯሯጡ ናቸው፡፡ ሕዝባዊ አመፅን መዳራጀተና ማምራት ሊመጣ የሚችለውን ጥቃት ለመቀበል መዘጋጀትን ይጠየቃል፡፡ ብረት አናነሳም ባይ የቃል ጋንዲዎችና የሰላም አባወራዎች ትግሉ የሚያስከትለውን መከራ ለመቀበል--ለመታሰር፤ለመደብደብ፤ለመሰቃየት ወዘተ--ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የቀን

ተቀንነቀ የለመዱት ኑሮ መዛባቱን መቃወሱን መቀበል ይገባቸዋል። ባዶ እጃቸውን የተቃውሞ ሰልፍ ሲመሩ ደረታቸውን ለጥይት መስጠትና በድፍረታቸውም አርአያ እንዲሆኑ የግድ ይሆናል። በተግባር እንዲመሩ እንጂ በባዶ ተኮፍሰው ወይም ምርጦች ነንና መሪ በሉን እንዳይሉ። ወያኔ ለምንረግመው ዐላማውም ቢሆን ጫካ ገብቷል። ደምቷል። ውጣ ውረዱን ቀምሷል። መለስ ዜናዊ ይህን ሁሉ መከራ አልተቀበለም ቢባል እንኳን ድርጅቱን ድርጅት ያሰኙት በወሬ ሳይሆን በትግል መሆኑ የሚካድ አይደለም። ዛሬ መለስ ዜናዊ ስልጣኑን ለመጠበቅ ሲል ትግልን አጥፊ ሰበካውን ሲያሰማ ተቃዋሚ ነን ባዮች የገደል ማሚቴ ከሆኑለት የሕዝብ ትግል መጎዳቱ አይቀሬ ነው።

የሕዝብ ድርጅቶች የሚታገሉትና መታገል የሚገባቸውም ከሕዝቡ የትግል ፍላጎት አንፃር እንጂ ጨቋኙ ቡድን በዘረጋላቸው መንገድ ወይም ፕሮግራም መሰረት መሆን የለበትም። ገዢውን ቡድን የማያስቀይምና የማያስቆጣ የትግል ዘዴ ብዙም የሚዘልቅ አይደለም። የመለስ ዜናዊን ቀሽት የማያሳርርና የማያቃጥል የተቃዋሚ መሪ ሊመረመር ይገባዋል። ገዢው መደብ ጥሩ ተቃዋሚ የሚለው ድርጅት ይዘቱን መመርመር ይኖርበታል። በአጭሩ ሀቀኛ የሕዝብ ድርጅት የሕዝብን ጥቅም በማስቀደም ለወያኔ የእሳት አለሎ ሆኖ መገኘት አለበት። አምባገነናዊ አገዛዝ በሰፈነበት ታማኝ ተቃዋሚ መሆን ተለጣፊ መሆን ነው። ሌላ ትርጉም የለውም። ድርጅቶች ታማኝነታቸው ለሕዝብ እንጂ ለገዢው ቡድን ወየመ ለባዕድ ኃይል ሊሆን አይችልም ወይም አይገባም ማለት ነው። ወያኔ በመለስ መሪነት የሕዝብ ሳይሆን የፀረ ሕቦች ጥውም አስጠባቂ ሆኖ ለሱዳንም ለሶማሊያም፤ ለቸሜሪካም ለሊቢያም ባመደር ሀገራችንን ለጨረታ አቅርቧል። ዓለም በአንድ ኀያል መንግስት መዳፍ ስር ገብታለች በሚልም ለዚሁ ባዕድ ኃይል ሎሌ በመሆን የሀገር ሳይሆን የባዕድ ጥቅምን እያስቀደመ ያለው ዛሬ መለስ ዜናዊ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎቹ ነን ከሚሉትም ውስጥ አንዳንዶቹ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። አንድ ድርጅት የሕዝብን ጥቅም ካስቀደመ እንዴት መታገል እንዳለበት ሆነ በምን መፈክር መንቀሳቀስ እንዳለበትም ግራ አይጋባም። ዓላማው የሕዝብን የበላይነትና መብት ማስረገጥ ነውና ከአቶ መለስ ዜናዊ ምስጋናንም ሆነ የፓርላማ ወንበር ለማግኘት እጥፍ ዘርጋ አይልም። ይህ ሁሉ ግልፅ መሆን አለበት።

ሕዝብ በህብረትና በስልት ለመታገል ድርጅት ወይም መደራጀት ያሻዋል። ብሶት ተጠራቅሞ በራሱ የስርዓት ለውጥ አያመጣም። እንባም ደምም ፈሰው ፈሰው በቃን እስኪወልዱ ሀገር ልትጠፋ ትቸላለች። መና የሚቀር የ ፁሐን ደም ባይኖርም ያልተደራጀ ሕዝብ የጭቆና ሰለባ ይሆናል። ወያኔ ይህን ያህል የቀለደብን አብረን ተባብረን መታገል ስላልቻልን ነው። ሀቀኛ ድርጅቶቻችንም በጊዜው አጋጣሚ ስለተዳከሙ ሊመሩን የ ሉበት ሁኔታ ገና እውን አልሆነም። እንደ ሕዝብም አቀፈን ደግፈናቸው ልንጀግን ገና ባለመቻላችን መለስ ዜናዊ በእብሪት ይቀልድብናል። በጋራ እንኳን ቆመን የመርጫውን ህግ ለውጥ አለበለዚያ ለማለት ስንጥር ሽብረክ ያሉ ክፍሎች የልብ ልብ ሰጥተውት ስቃያችንን አራዝመውታል። በአጭሩ የሕዝብ ጎራ አልጠራም። በታሪክ የሰማነው የፈሪ ተለይ የአስመሳይ ተለይ ጥሩምባ ገና አልተነፋም። ንዑሰ ክርስቲያኖች ከአፀደ መቅደሱ ውጡ የሚለው የቅዳሴው ደወል ዓይነት ማስፈለጉ ግን ይታያል። የሕዝብ ድርጅቶች ጎራቸውን መለየት አለባቸው። ጎራ መለየት ብቻ ሳይሆን የሕዝብን ትግል መምራትም መቻል ይጠበቅባቸዋል። ይህ ካልሆነ የድርጅት መተራመስ እውነትም እንደተፈራው ጠቃሚ ሳይሆን ጎጂ መሆኑ አይቀሬ ነው። ውድድራችን ለወያኔ ወንበርና ለባዕድ

ምስጋና ሳይሆን በትግሉ ሜዳ ማን ይበልጥ ሕዝብን አነሳሳ አታገለ ፤ ጀገነ፤ ታገለ በሚለው ቢሆን ለኢትዮጵያ ይበጃታል፡፡ ሕዝብም የነገ ዕጣውንና ሀገሩን ለማንም አሳልፎ ሳይሰጥ ለራሱና ለሀገሩ በገቢር ከሚታገሉለት ድርጅቶች ጎብ ተሰልፎ ታሪካዊ ትግሉን ከግብ ማድረስ ይጠበቅበታል፡፡ ከአኛ ከሕዝቦቿ ሌላ ለኢትዮጵያ የሚሞትላት ሊኖር አይችልምና፡፡